| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ልዩ ፡ ማስታወቂያ ። |
| ርእስ ፤ | *"ጥሪ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦<br>የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!<br>ለሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ ዐብር!"* |
| ደራሲ ፤ | የጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፥<br>ኢ..ሀ.ሥ.አ. ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቊ.2012-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ልዩ ፡ ማስታወቂያ

SPECIAL ANNOUNCEMENT | ANNONCE SPÉCIALE | مُطالَعة

ኢ ሀ ሥ አ

## ጥሪ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦
## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!
## ለሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ ዐብር!

---

መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ!

ከማንም ፡ በፊት ፥ በሥልጡንሕዝብናኽ ፥ *"ኢትዮጵያ"* ፡ የምትባል ፡ ቅድስት ፡ ሀገርኽን ፡ ከውነኽ ፥ በሀገራዊ ፡ እግዚእናኽ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ እየሠራኽና ፡ እያደስክ ፥ ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ባሕርያውያን ፡ መብቶችኽን ፡ እያስከበርክ ፥ እንሆ ፡ ለምእት ፡ ዓመታት ፥ በሐራ ፡ ሕዝብነትና ፡ በሐራ ፡ ሀገርነት ፡ ተከብረኽ ፡ ኖረኽባታል ።

በነዚህ ፡ ዘመናት ፡ የጥፋትና ፡ የጭቈና ፣ የውንብድናና ፡ የውርደት ፡ ወቅቶችም ፡ ተፈራርቀውብኻል ። ኾልጊዜም ፡ ቢኾን ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ መልሰኽ ፡ ያስከበርከውና ፥ ሀገርኽን ፡ መልሰኽ ፡ የዋጀኸው ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽን ፡ በሥልጣኔኽ ፣ በሥልጡንሕዝብናኽ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ አጽንተኸው ፡ በመታገልኽ ፡ ነበር ።

ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ በተለየ ፡ ኹኔታ ፥ ሰንደቅ ፡ ዐላማኽ ፡ ተዋርዶ ፥ እግዚእናኽ ፡ ተረምርሞ ፥ በገዛ ፡ ሀገርኽ ፡ *"ባይተዋር"* ፡ ተብለኽ ፥ ርስትኽን ፡ ተነጥቀኽ ፥ ባልፈቀድከው ፡ የ *"አፓርትሀይድ"* ፡ ሥርዐት ፡ ላጺያፊ ፡ አመሳሶ ፣ ላሠቃቂ ፡ የመብት ፡ ጥሰትና ፡ ለውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ተዳርገኽ ፡ ትገኛለኽ ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ ከ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ አጋማሽ ፡ ወዲህ ፥ የለውጥ ፡ ምኞት ፡ ተዋሽቶልኽ ፡ ነበር ። ከዓመት ፡ ተኩል ፡ በኋላ ፥ ኹኔታው ፡ ሲገመገም ፥ ከተዋሸልኽ ፡ *"ሥር ፡ ነቀል"* ፡ ለውጥ ፡ ውስጥ ፦

- ባንድ ፡ ወገን ፥ የቀድሞ ፡ እስረኞች ፡ በከፊል ፡ ሲፈቱ ፥ በሌላ ፡ ወገን ፥ *"መብታችን ፡ ይከበር"* ፡ ያሉ ፡ የሰብኣዊ ፡ መብት ፡ ተሚጋቾች ፡ *"አሸባሪዎች"* ፡ ተብለው ፡ ዛሬ ፡ ታስረዋል ፤
- *"የመጻፍና ፡ የመናገር ፡ መብት"* ፡ በዚያችው ፡ በዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ ሊደረገም ፡ ተቃርቧል ፤
- በውጭ ፡ የሚገኙ ፡ *"ተፎካካሪዎች"* ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ቢገቡም ፥ የታጠቁ ፡ ተገንጣዮች ፡ በእየ *"ክልሉ"* ፡ አናስደርስ ፡ ብለዋቸዋል ።

*"ግንቡን ፡ እንናድ ፤ ድልድዩን ፡ እንገንባ"* ፡ የሚለው ፡ የድለላ ፡ ቃልም ፡ ዛሬ ፡ ታጥፎ ፥ የጠላኸውን ፡ አገዛዝ ፡ በማሸጋገር ፣ ማእከላዊ ፡ መንግሥትን ፡ በማዳከም ፣ *"ክልሎችን"* ፡ በማጠናከር ፥ ከኹሉ ፡ የከፋ ፡ ደግሞ ፥ በእየ *"ክልሉ"* ፡ የ *"ዘር ፡ ማጽዳት"* ፡ ዘመቻን ፡ ከመቼውም ፡ የባሰ ፡ በማጠናከር ፡ ተተክቷል ። *"የሕግ ፡ የበላይነት"* ፡ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ቁና ፡ ተጥሎ ፥ ገዳይና ፡ አስገዳይ ፡ አላንዳች ፡ ሥጋት ፡ የሚፈነጩበት ፥ ተገዳይና ፡ ተበዳይ ፡ ፍትሕን ፡ ያጡበት ፡ አሳዛኝና ፡ አሥጊ ፡ ኹኔታ ፡ ተፈጥሯል ።

የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፥ አንተው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነኽ! ሌላ ፡ ማንም ፡ የለም! ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ መሥራትና ፡ በወደድከው ፡ ዐዳር ፡ ማደር ፡ ለማንም ፡ አሳልፈኽ ፡ የማትሰጠው ፡ የተቀደሰ ፡ የእግዚእናኽ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፦


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

- ተነሥ!
- ተደራጅ!
- ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽን ፡ አጽና!
- ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ ሥራ!
- ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥትኽን ፡ አቁም!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.) ፥ ይህኑ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማኽን ፡ እዳር ፡ ለማድረስ ፡ የተቋቋመ ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካልኽ ፡ ነውና ፥ ፈጥነኽ ፡ ዐብርለት!

*የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።*





©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።